# ማን ያውራ የነበረ #5

## ኢሕአፓ ሕዝባዊ ራዕዩ ።

ትግል ውድ ሕይወት የሚገበርበት፤ከባድ መከራን መቀበል ግድ የሚሆንበት ነውና ለምን ዓላማ፤ለማንስ ጥቅም መስዋዕት እንሆናለን፤እንሰቃያለን ለሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠቱ ቀዳሚ መሆን አለበት። ግለሰብን ለማንገስ ወይ ቁንጮ ለማድረግ ብቻ የሚደረግ ትግል አሳዛኝ ቢሆንም ቢያንስ ዓላማው ግልፅ ነው። ትግል ዓላማ ያሻዋል። የፕሮግራምን ነጥቦች ከበሳል ድርጅቶች ቀድቶ ከመደርደር ባሻገር ጠለቅ ያለና ራሱን የቻለ ራዕይ ያስፈልጋል። ለሕዝብና ለሀገር የሚደረግ ትግል ደግሞ ሕዝባዊ ራዕይ ከሌለው የትም አይደርስም። ኢሕአፓ ለ33 ዓመታት ፀንቶ የታገለው እስትንፋስ የሚሰጠውና የሚያጠናክረው ሕዝባዊ ራዕይ ስለነበረውና ስላለውም ነው። ስለዚህም ያለፉትን የኢሕአፓ አቅዋሞች ለመመርምር እንደቃጣነው ሁሉ ኢሕአፓ ሕዝባዊ ራዕዩ የሚለውንም መዳሰስ እንፈልጋለን።

ኢሕአፓ በ 1964 ዓ.ም የተመሰረተው መሬት ለአራሹ መብት ለሰርቶ አደሩ ሕዝብ ብሎ ለዓመታት ሲታገል ከነበረው እንቅስቃሴ ተወልዶ ነበር። መሰረቱ ሕዝባዊ ስለነበርም ራዕዩ የጥቂቶችን ኢትዮጵያ በትግል ለውጦ የብዙሀኑ ለማድረግ ነበር። የወቅቱ ስርዓት ለጥገና ለውጥ እንኳን ክፍት ባለመሆኑ በመፈንቅለ መንግስት ይወገድ ዘንድ ሙከራ ተደርጎበት እንደነበርም የሚታወስ ነው። ለዚህም ሙከራ የሰጠው ምላሽ ደፈሩኝ ያላቸውን መግደል ወይም አስከሬናቸውን ሳይቀር በአደባባይ መስቀል እንደነበረ በእነ ቢትወደድ መኮንን ነጋሽ፤ በእነ ገርማሜና መንግስቱ ንዋይ ላይ የወሰደው እርምጃ ፤ በእነ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ላይ የደረሰው ምስክር ነው። ተማሪዎችም በዚያን ጊዜ ለ "አባባ ጃንሆይ" አቤቱታ አቅራቢ እንጂ ተቃዋሚ አልነበሩም። ስርዓቱ ለውጥን ማስተናገድ ሲያቅተውና በአህጉራችንና በዓለም አቀፍ ደረጃም ይነፍስ የነበረው የለውጥ ነፋስ ኢትዮጵያንም ተነሺ ሲላት ታሪክ ውለታቸውን የማይረሳው ጀግናና ሀገር ወዳድ ምሁሮች አድህሪውን ስርዓት በስር ነቀል ለወጥ ለማስወገድ ትግል ጀመሩ። በነበረው የትግል ሁኔታና የኃይሎች አሰላለፍም በርዕዮት ወደ ግራ ማዘንበላቸው የግድ የነበረ ሲሆን ይህንን በመፃረር ሌላ አማራጭ ሆኖ የቀረበ አልነበረም። ብሄራዊ ራዕይ የነበረው ከበርቴ በቦታው ሰላልነበረ አቀባባይና የባዕድ ተለጣፊ ቅጥረኞች ሕዝብን የሚስብ አማራጭ ማቅረብ አልቻሉም። በሁሉም አንገብጋቢና ሀገራዊ ጥያቄዎች ላይ መልስ ሊሰጥ ደፍሮ የተነሳውና የቃጣው ተራማጁ ክፍል ስለነበር ባለው ርዕዮት መሰረት ምላሽ ሊሰጥ ሞክሯል።

ኢሕአፓ በዚህ ጊዜም ቢሆን ሕዝባዊ ራዕይን መሰረት አድርጎ ለሀገር ሉዓላዊነት ፀረ ኢምፔሪያሊሰተ ወይም ፀረ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ትግል ሲያካሂድ በመብት ደረጃ ደግሞ የአፄው ስርዓት ተወግዶ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ እንዲቋቋም ታግሏል። ይህ ትግሉ ከሕዝብ ትግል ጋር ተዳምሮ ለየካቲት 66 አብዮት መፈንዳት ምክንያት ሲሆን በአብዮቱም

ወቀት ኢሕአፓ ራዕዩን አጥፎና ሰርዞ ሹመት ይበቃኛል ብሎ በክህደትና በባንዳነት ጎዳና ሳይነጉድ የምርጥ መኮንኖች አገዛዝ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይተካ ብሎ ሕዝብን አነሳስቶ በሰላም መታገሉ ይታወሳል። የመኮንኖቹ ጥርቅምና የወቅቱ አጋሮቹም ኢሕአፓ ባካሄደው ፖለቲካዊ ትግል ስለተሸነፉም በኢሕአፓ ላይ ጦር አውጀው ሕዝብን የመፍጀት ዘመቻ መክፈታቸውም በታሪክ የተመዘገበ ነው። ዛሬ ታሪክን አጥፊዎችና ዳግም ወንጀል ፈፃሚዎች በሞላ ኢሕአፓ በደርግ ላይ በከተማ ጦርነት አወጀ ብለው ቢቀላምዱም ኢሕአፓ በሰላም ሲሰለፍና ሲታገል በየቀበሌው፣ በሰራተኛው ቀን (ሜይ ዴይና ሌሎችም ጊዜዎች)፣በጂማ፣በአዋሳ፣በአስበ ተፈሪ ወዘተ በዘመቱት በእነ አሊ ሙሳ፣በብቸና ሕዝብ ላይ ግፍ በፈፀሙት በእነ ሻለቃ እንዳለ ተሰማ ወዘተ ግድያው ተፋፍሞ ነበር። ደርጉ በመስከረም 20/1966 ባወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይዘቱና አቅጣጨው ምን እንደነበር ያሳየ ሲሆን ኢሕአፓ ለዓላማው በሰላም ሲታገል ቆይቶና አያሌ መስዋዕትነትን ከፍሎ እያለ የይፋ ጦርነት ሲታወጅበት ደግሞ ወደ ራስ መከላከሉ አምርቷል። ኢሕአፓ የሕዝቡን ራዕይ ለሹመት አሳልፎ ሳይሰጥም ደርጉ የሕዝበ ድርጅት ፅህፈት ቤት አባል ሆናችሁ ጭቆናዬን አጅቡልኝ ሲልም አሻፈረኝ ብሏል። በዚህም ሆነ በሌላ ጉዳዮች ሁሉ ኢሕአፓ ውሱን ድርጅታዊ ጥቅምን በማስቀደም የሕዝብን ጥቅም አሳልፎ ስላልሰጠ ለጠመንጃና ለድጋፍ ሲል ለሻዕቢያ አልተጎነበሰም፣ ለሚኒስቴርነት ሹመት ሲል ለመንግስቱ ኃይለ ማርያም አልሰገደም፣ ለባዕዳን ድጋፍ ሲል ኢትዮጵያን አልካደም።

ኢሕአፓ ሕዝባዊ ራዕዩን ጠብቆ የታገለ በመሆኑ ደግሞ ብዙ ስቃይን መከራ ደርሶበታል። ገዢ ነን ባዮችም፣ባዕዳንም፣ እነ ወያኔም ወግተውታል፣ አድምተወታል። ዛሬም ይህን የትግል ታሪኩን ሊያጠፉ የተነሱ ኢምንቶች ዘመቻ ከፍተውበታል። ይሀ ሁሉ ጥላቻ ፣ ይህ ሁሉ ዘመቻ ለምን ስንል ደግሞ የዘማቾቹን ማንነት በማጤን ብቻ መልሱን እናገኘዋለን። ትላንት በቀይ ሽብር ተሳትፈው ሕዝብን የፈጁና ያሰቃዩ፣ ፀረ ኢትዮጵያ የመለስ ሎሌዎች፡ ዴሞክራሲ ከመጣ ሕዝብ ለፍርድ ያቀርበናል ብለው የሰጉ ወንጀለኞች፣ ክደው ሕዝብን ድርጅትን የጎዱ ግለሰቦች፣ ለመለስ ዜናዊ ያደሩ ጥቅም አሳዳጆች ናቸው ዛሬ በኢሕአፓ ላይ የሚዘምቱት። ሕዝብ ግን ለኢሕአፓ ያለው አመለካከት ቀናና የድጋፍ ነው። በኢሕአፓ ትግል መብቱ ይከበር ሲባል አይቷል። በኢሕአፓ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሄረሰብ፣ ሀይማኖትና ፆታ ሳይለይ ሲታገል አይቷል። ኢሕአፓ ለጥቂቶችና ለምርጦች ጥቅም ሳይሆን ለብዙሀኑና ለጋራ ሀገር ሲዋደቅ ተመልክቷል። ኢሕአፓ ራዕዩ ሌላ ሳይሆን የሕዝብ መሆኑን በገቢር ማስመስከሩን መዝግቧል።።። የሕዝብ አለኝታና ደም መላሽ ሲል ኢሕአፓን የሚጠራውም አለምክንያት አይደለም። ዛሬ በተለይ በቃሉ የማይረጋ፣ወኔው ከክር የቀጠነ ፣ ለጥቅም ተሯሯጭ፣ ፅናት አልባ፣ መስዋዕትነትን ፈሪ፣ የምላስ አርበኛና የባዕድ ሎሌዎች የፖለቲካውን መድረክ ባጣበቡበት ወቅት የኢሕአፓ “ግትር” ሕዝባዊነት፣ ድፍረትና ቆራጥነት፣ሞት አይፈሬነት፣ ንፁህ ሀገር ወዳድነትና ፅናት ለሕዝብ በጎ ትዝታና ተስፋ ሰጪ ትውስት መሆኑ ግልፅ ነው። ኢሕአፓ በዓላማው መፀናቱን ግትርነት ወይም

በቅርቡ አንድ ምሁር እንዳለው በ "ድደብና"ም ሊፈርጁ የሚፈልጉ እንዳሉ ግልፅ ነው:: በአቅዋም መፅናት እንዲህ በአሉታዊ ከተፈረጀ ለመጣው ባለስልጣን ሁሉ መጎንበሱ ደግሞ ብልህነት መሆኑ ነው:: ህቁ ግን ሌላ ነው:: ለአፄውም ለአሜሪካም ማደር፣ ለደርግ አማካሪና ደጋፊ መሆን፣ ወያኔ ሲመጣ ደግሞ ልጆቼ ወይም ዴሞክራቶች ብሎ መደገፍ ነው በከፍተኛ አሳፋሪ ድድብናና አድርባይነት መመዘገብ ያለበት:: ይህን ዓይነቱ አቅዋም ቢስነት ነው ራፅይ አልባነትን የሚያሳይ--ማለትም መርሕ ስነ ምግባር አጥቶ ለሶስት ስርዓት ማደር ለምሳሌ:: ከዚያም ከሕዝብ ጎራ ለመደባለቅ ደግሞ መፍጨርጨር:: ኢሕአፓ ይህ ዓይነት ውሽልሽል መንፈስ ዝርም አይልበት:: ፅኑ ሆኖ የሚቆየው ደግሞ ጊዜ ይቀየር ያለውን አቅዋም ባለመቀየር ሳይሆን ሕዝብና ሀገርን ማስቀደም የሚለውን መርሁን ባለመለወጥ ነው:: ለደርግ አድሮ ደርግን መክዳት ከዚያም ለወያኔ አድሮና መለሰ ዜናዊን ደግፎ መሰለፍና ከዚያ ደግሞ ተቃዋሚ ነኝ ማለት ለምሳሌ ብልህነትን ሳይሆን ለሆድ ማደርን፣ መዋለልን፣ቋሚ ራዕይ ማጣትን አመልካች ነው:: ነጋ ጠባ ወደ ትቢያ እየተጣለ የሚነሳ ራዕይ ሕዝባዊ አይደለም::

ያለፈው ለመጪው ድልዳል ነውና የኢሕአፓ ራዕይ ዛሬም የሕዝብ ምኞትና ሕልም መሰረት ያደረገ ነው:: ዝንጀሮ መቀመጫዬን አለች እንደተባለው በቅድሚያ ጭንቀታችን ሀገራችንን ይመለከታል:: ወያኔ ሊያጠፋት የሚጥረውን ውድ ኢትዮጵያችንን በተመለከተ ኢሕአፓ የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ተከብሮ ፣እኩልነት ተረጋግጦ፣ አንድነቷ በዚሁ መሰረት እውን ሆኖ እንዲገኝ ይመኛል:: ይህም የሀገር አንድነት በመብትና በእኩልነት መረጋጋጥ ላይ ተገንብቶ ይገኝ የሚል አቅዋም ነው:: የኢሕአፓ ኢትዮጵያ ታላቅነቷ በሕዝቧ ስምረትና ብልፅግና፣ በመብቱ መከበርና መጠበቅ ላይ የሚከሰት ነው:: በተጨባጭ ደግሞ ኢሕአፓ የፌዴራል አወቃቀር ምናልባትም ለዚሁ ግብ የተሻለ አማራጭ ነው ብሎም ያምናል:: ይህንን አማራጭ ከደርግ ውድቀት በፊት ኤርትራም ችግር መፍቺያ ብሎ አቅርቦ እንደነበር የሚታወስ ነው:: ወደፊትም ቢሆን ኢሕአፓ ያለው ራዕይ ሰፋ ያለ የሕዝቦችን አንድነት የሚፈልግ በመሆኑ ሀገሮችና ሕዝቦች ተባብረው ካልቆሙ ኃያላን ሀገሮችን መቋቋም አይችሉም ባይ ነውና ከዛሬ የንዴትና የቂም በቀል ስሜት ባሻገር ህዝቦች የሚያብሩበትንና ከጦርነት አባዜ የሚላቀቁበትን መንገድ ይሻል:: ይህ ደግሞ በሁሉም መስክ ከትምክህትና ከጥበት መላቀቅን፣ ፅንፈኛና ጎጂ ከሆነው ብሄረተኛነት መራቅን የግድ የሚል ነው::

ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ያለው ራዕይ ዛሬ በዓለም ደረጃ የረሀብ መለያ ሆና ያለችውን የሚፍቅና የሚሰርዝ ነው:: በመሆኑም ትላንት አምኖበት የቅይጥ አኮኖሚ እንዳለው ሁሉ ዛሬ ደግሞ የሕዝብን ጥቅም የማይፃረርና ለከት ያላጠ የነፃ ገበያ ስርዓትን ይደግፋል:: በመሰረቱ በብሄራዊ ነጋዴዎችና ከበርቴዎች ላይ የቆመና የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ከፍ የሚያደርግ፣ ብዙሁኑን መረን ለለቀቀና ጭፍን ብዝበዛ የማይዳርግ ሆኖ ሀገሪቷን ግን የሚያለማና የሚያበለፅግ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴን ይመርጣል:: የሀገሪቷ ሀብትም ለባዕድ የማይጋዝበት

ወይም ቁልፍ የምርት ተቋሞቿ ለባዕድ አሳልፈው እንዳይሰጡም ፈላጊ ነው:: ሕዝብ በተለይም ሰርቶ አደሩ ሕዝበ የላቡ ተጠቃሚና በኤኮኖሚውም መስክ ወሳኝ እንዲሆን ይመኛል:: የኢሕአፓ የሀገር ግንባታ ራዕይ ሕዝብን ያቀፈና በሕዝብ ጥረት የሀገርን ግንባታ የሚፈልግ ብቻ ሳይሆን ሰርቶ አደሩም ሕዝብ በቅድሚያ የዕድገቱ ተጠቃሚ መሆን ይገባዋል የሚል ነው:: ከዚህ ባሻገር ደግሞ የኤኮኖሚው መስክም ለጉዳዩ ሙኅይም በሆኑ ዕቅድ አውጪዎች ወይም ዘራፊዎች እጅ እንዳይገባ ማድረግም ያሻል::

ኢሕአፓ እንደ ሕዝባዊ ድርጅት ራዕዮ ብሎ ሲሰለፍ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ የሀገራዊ ወይም ብሄራዊ ራዕይ ባለቤት ሕዝብ ራሱ ነውና የሕዝብ መብት መከበር ወሳኝ ነው ይላል:: ደጋግሞ እንደገለፀውም የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ያልተገደበ መሆን አለበት:: ስለሆነም በሰበብ አስባቡ የሕዝብን መብት ሊገድቡ ከሚሹ ኃይሎች ጋር አይስማማም:: በኢሕአፓ ራዕይ የሕዝብ የመደራጀት መብት፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች ነፃነት፣ የፅሁፍና የንግግር ነፃነት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ ወዘተ በሞላ ገደብ አልባ ናቸው:: መብት ሲልም ለብዙሀኑና ብዙሀኑ ለደገፉት አቅዋም ብቻ ሳይሆን በተለይም ተቃዋሚ ሀሳብ ላላቸው፣ ለህዳጣን፣በስልጣን ያለውን ኃይል ሊቃወሙ ለሚሹ ክፍሎች እውን የሚሆንና የሚረጋገጥ መብት ማለት ነው:: ማንም ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ አቅዋሙ የተነሳ ምንም ጥቃት እንዳይደርስበት፣ የስየል ወይም የጭካኔ ድብደባዎች በማንም እስረኛ ላይ እንዳይፈፀም ማገድ፣ የህፃናትን ሙሉ መብት ማስከበር፣ የሴቶችን ሙሉ መብት ማስከበር፣ ሀይማኖቶችን እኩልነት ማረጋገጥና መንግሰትና ሀይማኖትን መለየት ወዘተ ኢሕአፓ መብት ሲል የሚያካትታቸው ናቸው:: በኢትዮጵያ ምድር ሁሉም ኢትዮጵሮዊ የፍትህ ባለቤት ሆኖ፣በህግ ፊት እኩል ሆኖ፣ መብቱ ተከብሮ፣ሳይሸማቀቅ ቀና ብሎ በዜግነቱ ኮርቶ የሚኖርባትን ሀገር እውን ማድረግ:: ይህ የኢሕአፓ ራዕይ መንግስት የሚባለው ተቋም ለሕዝብ ታዛዥና ተገዢ መሆኑን የግድ የሚል ነው:: እስከዛሬ በሀገራችን መንግስት የተባለው ተቋም በሕዝብ ላይ የቆመ ፀረ ሕዝብ የሆነ ነውና የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መንግስት በሕዝብ የተመረጠ፣ በሕዝብ ሊወገድ ሊነሳ የሚችልና የሕዝብን ወሳኝነትና የበላይነት የማይነጥቅ ይሆናል:: ይህንንም ለማረጋገጥና ለመደንገግ ሕዝብ በወኪሎቹና በአዋቂዎች አስረቅቆ በውሳኔ ሕዝብ በነፃና በፍላጎት የሚያፀድቀው ሕገ መንግስት ይኖራል ማለት ነው::

ህፀናት በትምህርት ገበታ በመገኘት ፈንታ በመንገድ አዳሪነት ለልመና የሚዳረጉባት ኢትዮጵያ በኢሕአፓ ራዕይ ውስጥ የለችም:: ወጣት ሆኑ ሌሎች ሴቶች ለሴትኛ አዳሪነት እንዳይገደዱ፣ ሕዝብ የመጠለያ ቤት የማግኘት መብቱ እንዲጠበቅ፣ በበቂ የመመገብ ችሎታ እንዲኖረው፣ ለልጆቹ የትምህርት መብት ለቤተሰቡ የኑሮ የህይወት ዋስትና እንዲኖረው ማረጋጋጥ የኢሕአፓ ራዕይ አካል ነው:: የጤናው አገልግሎት ተስፋፍቶና አጥፊ በሽታዎች ተገድበው እንዲገኙ ማድረግ:: ጎጂ ባህሎችን ማስወገድ፣ ለአዛውንት እንክባካቤ ማድረግ፣ የሕዝብን ትስስር ማበረታታት፣ ማንም ሀገርን ጥሎ እንዳይሰደድ መጣር፣

የእስር ቤቶችን ቁጥር ማመንመን-መቀነስ። ራዕይን እየኖርነው ካለው ቅዠት መለየት ያሻል ማለት ነው፡ ሀገራችን በዜጎቿ ተከብራና ልጆቿን አስከብራ ትገኝ ዘንድ ደግሞ ከባዕድ ቁጥጥር ነፃ መሆኗ የግድ ነው።በመሬታችን የባዕድ ጦር ከቶም እንዳይሰፍር፤ የሀገራችን ሉዓላዊነት በባዕድ ኃይል ከቶም እንዳይደፈር ማረጋገጥ ማለት ነው። ይህም እንዳለ ሆኖ ከውጭ ሀገሮች ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነትን በማድረግና የአፍሪካ ሕዝበ የአንድነትን ትግል በመደገፍ ሀገራችን ሚናዋን እንደትወጣ አስፈላጊ ነው።

ሕዝባዊ ድርጅት ሕዝባዊ ራዕይ ያሻዋል። ይህንንም ራዕይ ከመቅፅበት በየታሪካ/ መታጠፊያ የሚጥለው ሳይሆን በፀና --አዎን በፀና--መንፈስ የሚያድሰው ነው። ወደ መሰረቱ ስንሄድ ደግሞ ዋናው ጉዳይ ኢትዮጵያን ለዜጎቿ መልሶ ማስረከብ ማለት ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ የልጆችዋ አይደለችም። ቀማኛና ጥፋቷን የሚመኝ ቡድን ከሕዝብ ነጥቆ ተቆጣጥሯታል። ለሕዝቧ ሲያል ገሀነም አድርጓታል። ይህንን እርግማን ማስወገድ ነው የኢሕአፓ ራዕይ። ለራሱ ውሱን የፖለቲካ ስልጣን መዋደቅ ሳይሆን ሕዝብ መብትና የሀገር ባለቤትነት መታገል። ራዕያቸው ቤተ መንግስት አዳራሽ ላይ ከሚዋልለው ወይም ከሹመትና ገንዘብ ዙሪያ አለሁ አለሁ ከሚለው ክፍሎች ኢሕአፓ የተለየ መሆኑን ባካሄደው ትግል የደም ዋጋ ከፍሎ አስመስክሯል።

ኢሕአፓ ዛሬ ዋናው ተልዕኮ ሕዝባዊ ራዕዩን መጠበቅና አለመበረዝ፤ አለመሸርሸር ነው። ፍራንክ ሲያቃጭል መርሕን አለመርሳት። በፅናት--አዎን በፅናት -- ግትር ድርቅ ብሎ ሕዝባዊ ራዕይን እውን ማድረግ። ማን ያውራ የታገለ ፤ለሕዝብ ሲል የተሰዋ፤ መከራ የተቀበለና ሕዝባዊ ራዕዩን ያልካደ ።

.............................................//////..........................................
.